# በአኹኑ ሰዓት ፡ በደቡብ አፍሪቃ አገር ፡ በኢትዮጵያውያትና በኢትዮጵያውያን ላይ ፡ እየደረሰ ስላለው ሰቆቃ ፡ ተጠያቂው ማን ነው? መፍትሔውስ ምንድር ነው?

ይህንኑ አስመልክቶ፡ በኢትዮጵያውያትና በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ አኹንም፡ የ"እግዚኦታ" እና "ፈኑ እዴከ እምአርያም!"፡ ማለትም፡ "እጅህን ከአርያም ላክ!"[፩] የሚሉ፡ አሳፋሪና ዓመፀኛ ጸሎቶችና ልመናዎች፥ ምልጃዎችና ምሕላዎች እየቀረቡ ይገኛሉ።

ነገር ግን፡ ይህ እየኾነ ያለው፡ የነቢዩ የልመና መዝሙር፡ ዘለዓለማዊውን ምላሽ አግኝቶ፡ በኪዳነምረቱ፡ የውዳሴ ማርያም ምስጋናችን እንኳ፡ "ተፈሣሕ! ወተሓሠይ! ኦ ዘመደ ዕጓለ እምሕያው፤ እስመ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም፤ ወመጠወ፡ ወልዶ ዋሕደ፡ ከመ ይሕየው ኵሉ ዘየአምን ቦቱ እስከ ለዓለም፤ ፈነወ ለነ መዝራእቶ ልዑል። ንዌድሰኪ፡ ኦ ቅድስት! እስመ በትንባሌኪ ዘእም፡ ረከብነ ሣህለ ወልድኪ ዘለዓለም።"

ማለትም፡ "የሰው ወገን የኾንህ ፍጡር ኹሉ፡ እጅግ ደስ ይበልህ! ሓሤትም አድርግ! እግዚአብሔር አብ፡ ዓለሙን ወድዶታልና፤ በእርሱ የሚያምን ኹሉ፡ ለዘለዓለም ይድን፥ ሕያውም ኾኖ ይኖር ዘንድ፡ አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በቤዛነት አሳልፎ ሰጥቶለታል፤ እግዚአብሔር አብ፡ እንዲህ አድርጎ፡ ኃያል ክንዱን ሰደደልን። ቅድስት ሆይ! የእናትነት ምልጃሽ፡ የልጅሽን ይቅርታ ስላስገኘልን፡ እናወድስሻለን።"[፪] በማለት፡ የምናመሰግን መኾኑ እየታወቀ ነው።

በመኾኑም፡ ከዓመታት በፊት፡ "ፈደዩኒ እኪተ፡ ህየንተ ሠናይት"፡ ማለትም "ስለበጎ፡ ክፋትን መለሱልኝ"[፫] በሚል ርእስ፡ በሳዑዲ የዓረብ አገር፡ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ላይ የተፈጸመውን ግፍ አስመልክቶ ያወጣነውን ጽሑፍ፥ ይህው፡ አኹንም ለተፈጠረው አሠቃቂ ክሥተት፡ መፍረጃ እንዲኾን ቀርቧልና፡ ይኽውላችሁ፡ በአትኵሮት ተመልከቱት!



ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፡ ኢትዮጵያውያንም፤ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን፡ ለማስረዳት፡
የ "ኢትዮጵያ" እና የ "ኢትዮጵያውያን" የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ።
ለተጨማሪ እውነት ጎዋ ሰሌዳችንን ይጎብኙ። http://www.ethiopiathekingdomofgod.org

To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God;
and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians
For further details on the "Truth" visit our website: http://www.ethiopiathekingdomofgod.org

**መቼም፡ የጕድለቱና የስሕተቱ፥ የጥፋቱና የችግሩ አመንጭዎች ብቻ ሳይኾኑ፡ ይኸው፡ ሰለባዎችም ጭምር እስከመኾን የደረሱት፡ እየራሳቸው፡ ወገኖቻችን የኾኑት፡ ሰብኣውያን ፍጡሮች እንጂ፡ ከቸሩ ፈጣሪያችን ልዑል እግዚአብሔር እና ከቅድስት እናቱ ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም፡ ሳይደረግልን የቀረ፡ አንዳችም ጸጋና በረከት እንደሌለ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት እንደተገነዘብነው እናምናለን።**

**እውነታው፡ ይህ ኾኖ ሣለ፡ በዚህ ረገድ፡ በእኛ በኩል፡ የሱባኤና የምሕላ ጸሎታችንን (ምስጋናችንን)፡ ለአርባ ዓመታት፡ ለአንዲት አፍታ እንኳ ሳናስታጕል፡ እስካኹን እንደቀጠልን ኹሉ፡ አኹንና ወደፊትም፡ ይህንኑ ትጋሃችንን እንደምንቀጥል፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ በኪዳናውያንና በኪዳናውያት ዘንድ የታወቀ ነው።**

**ታዲያ! የመከራው ጽዋ ተቀባዮች ኹሉ፥ መሰሎቻቸው ጭምር፡ አኹንና ከዚህ በኋላ፡ ምን ለማድረግ እያሰቡ ነው? ካለፈው አደገኛና ከባድ የክህደትና የዓመፅ ጥፋታቸው፡ በእውነተኛ ንስሓ እየተጸጸቱ፡ ወደእውነተኛው የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታቸውና ማንነታቸው እየራሳቸውን ሊመልሱ ወስነዋልን? ቈርጠዋልን? ተዘጋጅተዋልን?**

**እንግዴህ፡ ልናይ፥ ምስክሮችም ልንኾን ነው።**

## ***<u>የጥቅስ ዝርዝር ፦</u>***

***፩፡ (መዝ. ምዕ. ፩፻፵፫፥ ቍ. ፯፤ ከግእዙ የቅዱስ መጽሐፍ አብነት።)***
***፪፡(የሰኞ ውዳሴ ማርያም፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፡ ሦስተኛ መጽሐፍ፤ በንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፤ ገጽ ፵፯።)***
***፫፡(መዝ. ምዕ. ፴፩፥ ቍ. ፲፩፤ ከግእዙ የቅዱስ መጽሐፍ አብነት።)***



ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፡ ኢትዮጵያውያንም፤ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን፡ ለማስረዳት፡
የ “ኢትዮጵያ” እና የ “ኢትዮጵያውያን” የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ።
ለተጨማሪ እውነት ኅዋ ሰሌዳችንን ይጎብኙ። http://www.ethiopiathekingdomofgod.org

To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God;
and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians
For further details on the “Truth” visit our website: http://www.ethiopiathekingdomofgod.org